# ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የአጼ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ነው ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ተም
ላቆ ያደገ መስፍን በመሆኑ በልጅነቱም "....በጣም ጠጪ ነበረ ።...." ይለዋል
ሞስሌ በመጽሐፉ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን እንደያዙ ትግራይን ለሁለት ከፍለው ለራስ
ስዩምና ለኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በገዢነት ሰጧቸው ። በዚያም ላይ ቀዳማዊ ኃይለ
ሥላሴ ገና ለጋብቻ ያልደረሰች ልጃቸውን ዘነበወርቅን (ብዙ ፀሐፊዎች 13 ዓመቷ
ነበረ ይላሉ) ለኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በሚስትነት ዳሩለት "...ስካራም ባልዋ እያበሳ
ጨና እየደበደበ ሊያኖራት አልቻለም...." ይላል ሞስሌ ። ልጅቱም በወሊድ ምክ
ንያት ሞተች ።

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ "ግዛት አንሶኛልና ትግራይ በሙሉ ተጠቃሎ ይሰጠኝ"
በማለት አመለከተ ። ንጉሱም "ሁሉን ለማስተዳደር አትችልምና ከስዩም ጋር እየተረ
ዳዳችሁ ግዙ" አሉት ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በእማችነቱ ሁልጊዜ ወደ አዲስ አበባ
ይመላለሳል ። ወደ አዲስ አበባ የሚመላለሰውም በአስመራ ዞሮ በመርከብ ወደጂ
ቡቲ ሄዶ ፤ ከጂቡቲ በባቡር ተሳፍሮ አዲስ አበባ ይገባል ። ኤርትራ ወሰን በሚደርስ
በት ጊዜ የኢጣሊያ መኪና ተቀብሎ አስመራ ያገባዋል ። ሲመለስም ከባህር ጠረፍ
እስከ ትግራይ ወሰን በኢጣሊያ መኪና ይጓዛል ።

ደቦኖ በመጽሐፉ "....ጉግሳ የንጉሠ ነገሥቱ ሴት ልጅ ባል ነው ። ግን ያመፀ
አመፀኛ ነው ።.... በትግሬ በተሾሙት በራስ ስዩምና በሱ መሀል ቅራኔ አለ ።....የስለላ
ጓዶቻችንና እድዋ ያለውም ቆንሲላችን ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኛ ወገን እንዲሆን
አድርገውታል ።....አስመራ መጥቶ የኛ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ሹመት እንድሰጠው
ጠየቀኝ ፡ ....ከኢትዮጵያ ጋር ግጭቱን እስትንጀምር ድረስ እሺ እያልኩ አቆየሁት ።
....እንቁላል ለመጥበስ መጥበሻውን ከማዘጋጀታችን በፊት እንቁላሉን እንዳልሰብር
ብዬ ነው ። ስለዚህ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን ግድየለም ታገስ ብቻ....ቀኑ በደረሰ ጊዜ
ያልከውን ሁሉ አደርግልሃለሁ እያልኩ አቆየሁት ።..." ይላል ።

በአሥመራ የኢትዮጵያ ቆንሲል የነበሩት ወዳጆ ዓሊ ወደ አዲስ አበባ መጥ
ተው ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኢጣሊያኖች ጋር መወዳጀቱንና ከኢጣሊያኖችም ደሞዝ
እንደሚከፈለው በበቂ ማስረጃ አስረድተው ለንጉሡ አመለከቱ ። ንጉሠ ነገሥቱም
"...አሁን ያለው የኢትዮጵያ መኳንንት አብዛኛው ከኢጣሊያ ገንዘብ ይቀበላል ።
ይህም የኢጣሊያን ኢኮኖሚ ለመጉዳት እንጂ እኛን ለመክዳት አይደለም ። ሁሉም
ከኛው ጋር ናቸውና የኃይለ ሥላሴ ጉግሳም እንደዚሁ ነው ..." ብለው የወዳጆ
ዓሊን ሪፖርት ሳይቀበሉ ቀሩ ።

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ጦርነቱ ሊነሳ አቅራቢያ መስከረም 28 ቀን ከአዲስ አበባ
ጋር የሚያገናኘውን የስልክ መስመር በሙሉ በጣጥሶ በወታደሮቹ ታጅቦ የአሥመራ
ጉዞውን ጀመረ ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ወደ ኢጣሊያኖች ከመግባቱ በፊት 12000 ወታ
ደሮች ነበሩት ። ኢትዮጵያን ከድቶ ወደ ኢጣሊያ ሲገባ ግን እሱንም ሠራዊቱ ከድ
ቶት ታጅቦ የገባው በአንድ ሺ ወታደር ያህል ነው ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ እዳጋ
ሐሙስ ላለው የኢጣሊያ ጦር እጁን ሲሰጥ ለኢጣሊያ መንግሥት ከልብ ለማገልገል
መምጣቱን ነገረ ።

ደቦኖ በመጽሐፉ ስለ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ አመጣጥ ሲገልጥ "....ኦቶብሬ 8 ቀን ጀኔራል ሳንቲኒ በላከብኝ መልእክት ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኛ እርዳታ መፈለጉንና መቀሌ ውስጥ 7000 ሰዎች ይዞ የተቀመጠውን ደጃዝማች ኃይሉ ከበደን ለመውጋት መጠየቁን ላከብኝ ። ...ኦክቶብሬ 10 ቀን ጧት ጀኔራል ሳንቲኒ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎቹን ይዞ በኛ መስመር ለማለፍ ጠይቋልና ምን ላድርግ? ብሎ ላከብኝ። እኔም መምጣቱን ይምጣ ፤ ግን አንድ ዓይንህን ጣልበት አልኩት ።...ቀትር ሲሆን የአየር ክፍላችን እንዳስረዳኝ በረጅም ሰልፍ በሰላም እንደሚጓዝና በጓዙም ውስጥ ከብቶች መኖራቸውንና ጉዞውም ከመቀሌ ተነስቶ በአዲግራት በኩል ለማለፍ ከመሀል መድረሱን ነገሩኝ ። በአራት (በኛ 10) ሰዓት ከአንደኛ ክፍለ ጦር በራዲዮ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ 1200 ሰዎች ፤ 8 ጥሩ መትረየሶች ይዞ አዲግራት መግባቱን ነገሩኝ ። ይህንንም ወደ ሮም ሳስታውቅ 10 000 ወታደሮች አሉት የተባለው እያባ ዙት ነው ብዬ መምጣቱን ነገርኩ ። ለጀኔራል ሳንቲኒም በሚቀጥለው ቀን ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኔ ዘንድ መጥቶ እንድንገናኝ እንዲያደርግ በቴሌግራም አሳወቅሁት ።

"ኦቶብሬ 12 ቀን በ11 (በኛ 5) ሰዓት ኮአቲት ደረሰ ። እኔም በጐጆዬ ውስጥ ተቀበልኩት ። እሱም መከፋቱን ነገረኝ ። ስለ ጉዳዩም አንዳንድ ፍንጭ አጫወተኝ ። በአበሻ ውስጥ ጦርነት የሚፈልግ ሰው እንደሌለና ጦርነቱን የሚፈልግ ንጉሡ ብቻ መሆኑን ነገረኝ... አሁን ፈጥናችሁ መቀሌን ብትይዙ በሰላም ገብታችሁ ትቀመጣ ላችሁ አለኝ ። እኔም ይሄን ለመወሰን የምችለው አቀርዳትን ጐብኝቼ ስመለስ ነው አልኩት ። ከዚያ በኋላ ስለኛ ወታደሮች ያለውን አስተያየት ጠየቅሁት ።

"እጅግ በጣም ታላቅ ዝግጅት ነው አለኝ ። በተለይ የሠራነው መንገድ እንዳስ ደሰተው ነገረኝ ። ...ሰዎችህ አሁን ባንተ ላይ ሙሉ እምነት አላቸውን? አልኩት ። እሱም በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ እንደነገርኳችሁ በጣም ጥሩ ነገር የሚሆነው በተቻለ ፍጥነት መቀሌ ብትገቡ ነው አለኝ ።..." ይለዋል ።

የዚህ ሰው መክዳት የኢትዮጵያን ጦር በብዙ መንገድ ጐድቷል ። አዲስ አበባ በሚመጣበት ጊዜና መቀሌም ሆኖ ንጉሠ ነገሥቱ የጦሩን ምስጢር ያጫውቱትና ያማክሩት ስለነበረ የኢትዮጵያን ጦር ሁኔታ በዝርዝር ያውቀዋል ። ይህንንም የሚያ ውቀውን የኢትዮጵያን ጦር ሁኔታ በዝርዝር ለዶቦኖ ነግሯል ። ኢንጂኘር ፌርናርድ ቤትሪ የተባለ የስዊስ ሰው ከደሴ አዲስ አበባ ድረስ የሚሠራው መንገድ ፕላን ነበ ረውና አብሮ ከድቶ ፕላኑንና መሰናክሎቹን ሁሉ የሚገልፀውን መመሪያ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ለዶቦኖ ሰጠ ። መቀሌ ድረስም ያለ ምንም ችግር በሱ መሪነት ኢጣሊያኖች መጓዝ እንደሚችሉ አስረዳ ። ራስ ስዩምም ምንም መከታና ረዳት ስለሌላቸው ከዋና ከተማቸው ከአድዋ በቀላሉ መግባት እንደሚቻል ለዶቦኖ አጫወተው ።

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ባልከዱት ጥቂት ወታደሮቹ ታጅቦ ፤ ካኪ ልብሱን ለብሶ ፤ በሠራዊቱም መሀል ሃያ መትረየስ ፤ አራት የተራራ መድፍና ሁለት መለስተኛ ፀረ አይሮፕላን መትረየስ ይዞ ከደቦኖ ጋር ሲገናኝ ጀኔራል ደቦኖ ምስጢሩን ሁሉ ከሰማ በኋላ በኢጣሊያ ንጉስ በቪክቶር አማኑኤል ስም የትግራይ ጠቅላይ ገዥ ብሎ ሾመው።

ስለ ሹመቱ ጉዳይ ደቦኖ ሲገልጽ "...ሙሶሊኒ በቴሌግራም ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን የትግሬ ጠቅላይ ገዥ ብዬ እንድሾመው አሳወቀኝ ። አሳቡ ጥሩ አሳብ ነው ። ነገር ግን እኔ እንዳጣራሁት ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሕዝብ የሚያቅፈው ትልቅ ሰው አይደለም ። ተዋጊም አይደለም ።.... እንደ አባቱ እንኳ የማስተዳደር ችሎታ የለውም ። ቢሆንም ብዙ ወታደሮች በተሰበሰቡበት በንጉሣችን ስም ሹመቱን አወ ጅሁለት...." ብሏል ።

ከእኚህ ሰው ጋር በ1967 ዓም ተገናኝተን ስንጫወት "....በሰላም በግብርና እያረስሁ ለመኖር እንጂ ኢትዮጵያን ለመጉዳት አልከዳሁም..." ብለውኛል ። ውሸታቸውን ነው እንጂ በአምስቱ የፋሺስት ዘመናት የሠሩዋቸውና በየጊዜው የሚ

ሾለሟቸውን መዳሊያዎች የሚያወሱ የኢጣሊያ ጊዜ ጋዜጦች ከኔ ዘንድ በብዛት አሉ ።

ሙሶሊኒ ለዶቦኖ በሰጠው መልስ "…ደም መፍሰስ የሌለበት በፕሮፓጋንዳ ብቻ ድል አድርገው…" ስላለ በዶቦኖ ትእዛዝ ፤ በኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰባኪነት አን ዳንድ የትግራይ ሹማምንት ለኢጣሊያ ገቡ ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳም ካኪውን ለብሶ ፤ በቀይ ሐር ጥብጣብ በግራና በቀኝ ቁልቁል የተሰመረበትን ጠባብ ሱሪውን ታጥቆ ፤ ረጅም ቧት ጫማ አድርጎ ፤ የኢጣሊያኖችን ጠርቡሽ(ባርኔጣ) ራሱ ላይ ደፍቶ በአስ መራ ከተማ ውስጥ እየተዘዋወረ ለሕዝብ ይታይ ጀመር ። ኢጣሊያውያኖችም በየቀኑ ሽቶና ሻምፓኝ ይሰጡት ጀመር ።

ጦርነቱ በተነሳ ጊዜ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ለኢጣሊያኖች እጅግ ጠቃሚ ሥራ የሠራና ቀንደኛ ተዋጊ ነበር ። በተለይም በመንገድ መምራት በኩል ብዙ አገልግሏል ። ይህንንም በመጠኑም ቢሆን ባለፈው ትርካዬ ውስጥ አልፎ አልፎ ገልጫለሁ ። እልፎ አልፎ ወደፊትም እገልጣለሁ ።

# የኢትዮጵያ ጦር

የኢትዮጵያን ወታደር ብዛት ዊልያም ማኪን ሲገልጽ ከነጀሌው 700 000 ያደርሰውና "...ካኪ ለብሶ የሚታየው የሰለጠነው ወታደር ግን 25,000 ይሆናል" ይላል ። ይህ እንግዲህ በጠቅላላ ለኢጣሊያ የተሰለፈው ጦር ነው ። ኢጣሊያኖች በሰጡት ግምት የኢትዮጵያ ወታደር 350 000 ነው ይሉና 400 000 ጠመንጃ በያይነቱ ፤ 200 መድፍ ፤ አምሳ ቀላልና ከባድ ኦርሊኮን (ፀረ አይሮፕላን) አላቸው ብለዋል ። ሊዎናርድ ሞስሌ እንደፃፈው ደግሞ የኢትዮጵያ ጦር 200 ትናንሽ የተለያዩ መድፎች ፤ ለእያንዳንዱ መድፍም 500 ጥይት ፤ 3500 መትረየስ ፤ 15 አይሮፕላን ፤ ለስምንት ወር ከሚበቃ ቤንዚን ጋር ኢትዮጵያውያን ነበራቸው ብሏል ።

ወደፊት በየጦሩ ቦታ ለመግለጽ እንደምሞክረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ለመሆን የበቃው በጦር መሪዎቹ የአመራር ችሎታ ማነስና ጠላትን በመናቃቸው ነው ። እያንዳንዱ መኳንንትም የርስ በርስ ቁርሾ ስላለበት አንዱ አንዱን በማጋፈጥ ፤ በጦር ሜዳ ላይ ሹም ሽር በማድረግ ፤ ለዘውዱና ለሥልጣን የነበራቸው ሽሚያ ሁሉ ተጨምሮ ሕዝቡን ባንድነት ሊያስተባብረው ባለመቻሉ ኢጣሊያ ድል ለማድረግ ቻለች ። ይህን የኢጣሊያ ጦር መሪዎች ሁሉ አምነውበታል ።

የዚያን ጊዜውን የሁሉንም አሳብ አሁን መናገር አይቻልም እንጂ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ጦር መሪ ምን ዓይነት ስህተት እንዳደረገ አለፍ አለፍ እያልን በመጠኑ እናየዋለን ። የኢትዮጵያ ጦር አማካሪ የነበረው ሩሲያዊው ኮሎኔል ኮኖቫሎፍ (T.E. Konovaloff) በመጽሐፉ "... ራስ ሥዩም የተከበሩና ክብራቸውን የሚጠብቁ ሰው ናቸው ...የቶፖግራፊ ካርታ ሳሳያቸው በዚህ ጉዳይ አትጨነቅ ። አልፈልገውም ። የካርታ ጉዳይ ስሜት ያለው ራስ ካሣ ነው ። በእነሱም ላይ ካርታ ብቻ ሲመለከት ብዙ ሰዓት ያጠፋል ። ለኔ ግን ምንም ስሜት አይሰጡኝም ። በዚህ ምክንያትም እባክህ አታስቸግረኝ ይሉኛል ..." ሲል ጽፏል ። ኮኖቫሎፍ የሚያቀርበው ካርታ የኢጣሊያ ጦር በየት ቢመጣ በየት በኩል መግጠም እንደሚቻል የሚያስረዳ ነበር ። ግን ተቀባይ አጥቶ ጦሩ እንደ ዝንጀሮ ገደል እየቧጠጠ እንዲዋጋና እንዲያልቅ ሆነ ።

በዶቦኖ ቦታ የተተካው ዋናው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ማረሻል ባዶሊዮም ቢሆን በኋላ ጊዜ ባሳተመው መጽሐፉ የኢትዮጵያውያንን ጦር መሪዎች ሁኔታ ገልጾታል ። "...የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች በሙሉ የጦር አዛዥነት ችሎታ ፈጽሞ የላቸውም... ጉዳዩን ሁሉ በቀላሉ የሚገምቱና የሚመፃደቁ ናቸው..." ብሏል ።

የባዶሊዮ የቅርብ ረዳት የነበረው ጄኔራል ኳሪኖ አርሜሊኒ (Quivrino Armellini) ስለኢትዮጵያውያን ጦር መሪዎች ሲገልጽ "....ራስ ካሣ ፤ ራስ ሙሉጌታ ፤ ራስ ስዩምና ራስ እምሩ ስለ ጦርነት የተማሩት ትምህርት የለም ።... ታላቅ ሰውነታቸው ብቻ ለጦር አዝማችነት አበቃቸው ። ...ምንም አይነት የጦር ትምህርት ሳይኖራቸው ፤ በዘመናዊ የጦር ትምህርት የሰለጠነውን ወታደር ፤ ዘመናዊውን መሣሪያና ዘመናዊ ጦር አዛዦችን እንዲገጥሙ ታዘዙ ። ይህ ነው ድል ለመሆን ያበቃቸው ምክንያት..." ብሏል ።

ባዶሊዮ ስለራስ ካሣ ሲጽፍ "... የማዘዝ ልምድ የለውም ። በደህና ጦርነት ቦታ ውሎ ደህና ውጊያ እንኳ አላየም ። ሌላው ቀርቶ የራሱን ወታደሮች እንኳን ሥራ ማሠራት አይችልም ። ወታደሮቹ ግን ምርጥ ምርጦች ናቸው ። ባለፈውም ሆነ አሁን የአበሻ ጦር መሪዎች ከፊታቸው ካለው ጠላት ይልቅ ከኋላ የቀረውን ወዳ

ጃቸውን ይፈራሉ ። በዚህም ፍራቻ ምክንያት ያላቸውን ኃይል ሁሉ ባንድነት ሰብስ
በው ከጠላት ጋር አይታገሉበትም ። ከኃይላቸው ግማሹ ተከፍሎ በመንደር ይቀርና
የጌታውን ክብር እንዲጠብቅ ይደረጋል …” ብሏል ። በሌላው የመጽሐፉ ገጽ ላይ
ደግሞ ባዶሊዮ ይህንኑ ጉዳይ አንስቶ “…በኢትዮጵያውያን ጦር መሪዎች መሀል
መለያየትና የውስጥ መጠራጠር እንደተፈጠረው ሁሉ ወታደሩም ጌታውን እየተከ
ተለ ተሽካክሯል ። ለዚህ ሁሉ መለያየት ያበቁት ንጉሡ ናቸው ።… ራስ ስዩም ፤
የግል ጉዳይ የሆነ የማዕረግ ነገር ቂም አለባቸው። ራስ ካሣ ጥሩ የቤተ ክርስቲያን
ሰው ናቸው ። ሙሉጌታ ጦረኛና በጦር ያደገ ሰው ነው ። በዚህም በጦረኛነቱ ምክን
ያት ጠቅላይ የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ ሆኖ ተሾሞ ነበር …” ብሏል ።

ባዶሊዮ ራስ ሙሉጌታን “… ተሾሞ ነበር…” ያለው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር
አዛዥ የነበሩት ራስ ሙሉጌታ ተሽረው ራስ ካሣ ከተሾሙ በኋላ ያተተው ነው ። ስለራስ
ሙሉጌታ መሻርና ስለራስ ካሣ መሾም ባርከር ሲጽፍ “…ንጉሡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ከታላላቅ ሰዎች የተወለዱ ናቸው እንጂ የጦር አመራር ችሎታ ያላቸው አይደሉም ።
ለመጀመሪያ ጊዜ ጦርነቱ ውስጥ ለመግባት ደሴ ሲደርሱ የሥራ መጀመሪያ ያደረጉት
ራስ ሙሉጌታን ሽረው የቅርብ ወዳጃቸውን ራስ ካሣን መሾም ነበር ። የጦር ሚኒ
ስትሩ (ራስ ሙሉጌታ) የታወቀ ጐበዝ ሰው ነበር ። የሚጠበቀውና የሚፈራውም
የሱ ጦር አመራር ነበር ። የወታደሮች ወታደር ነበር ። ራስ ካሣ ግን ምንም የጦር
ጥበብ የማያውቅ ሰው ነው ። ከነገሥታት ትውልድና በፖለቲካም ተሰሚነት ስላለው
ብቻ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ሆነ ። ለዚህ ነው ባዶሊዮ የሙሉጌታን መሻርና የካሣን
መሾም ሲሰማ የተደሰተው ።…” ካለ በኋላ በሌላ የመጽሐፉ ገጽ ደግሞ “… ሙሉ
ጌታ ተሽሮ ካሣ ሲሾም አምባራዶም ያለው ሙሉጌታና ጐንደር ያለው እምሩ
የካሣን ትእዛዝ ላለመስማት ጆሮአቸውን ደፈኑ ። ሙሉጌታ የሚደርሰውን ትእዛዝ
እንዳልሰማ እየሆነ ምንም የሰማሁት የለም ይላል ። እምሩም የተነሳብኝን ያገር ውስጥ
ሽፍታ በመከላከል ላይ ነኝ እያለ አይታዘዝም ። የካሣ ትእዛዝ ተቀባይ አጣ ። እን
ዚህ ሁለት ታላላቅ ጦረኞች የሚያስቡት አሳብ ካሣ የሚገጥመውን ገጥም እንዲ
ቀረድና ከፍ ያደረገው የንጉሡ ዓይን ዝቅ እንዲያደርገው ነው…” በማለት ይተነ
ትናል ።


ባርከር “…የተፈራው ጦር የሙሉጌታ ነበር…” ያለው እውነቱን ነው ። ይህን
ነገር የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ባዶሊዮም በመጽሐፉ እንዲህ ሲል
ይገልፀዋል “…የጦር ሚኒስትሩ ሽማግሌው ራስ ሙሉጌታ በአድዋ ዘመቻ ክንዱን
ያሳየ በመሆኑ የኢትዮጵያን ጦር ፈርተን ብዙ መሣሪያ አከማችተን ነበር ። ጦር
ነቱ እንደተጀመረ ንጉሡ ፤ ራስ ሙሉጌታን ሽረው ቄሱን ራስ ካሣን የጦር ሚኒ
ስትር አድርገው በመሾማቸው የኢጣሊያ ጦር በቀላሉ ድል እንደሚያደርግ ገብቶን
ተደስትን ። በመኳንንቱ መሐል ባለው የርስ በርስ ያለ መግባባትም ተጠቀምን ። ንጉ
ሡም የራስ ሙሉጌታን ሠራዊት እንዲከዳ ስላደረጉ ራስ ሙሉጌታን ከጥቂት ከተረ
ፉት ታማኝ ወታደሮቹ ጋር አዳል በረሃ ውስጥ አግኝተን በአይሮፕላን መትረየስ
ገደልነው ። በዚህም በሙሉጌታ ሞት የኢትዮጵያውያንን ሞራል ሰበርነው…”

በኢትዮጵያውያን መሀል ባለው ያለመግባባትና መለያየት ምክንያት ከውጭ
አገር ኢትዮጵያን ለመርዳት የተነሱና በኢጣሊያ ግፈኛነት የተበሳጩ የውጭ አገር
ሰዎች ሁሉ ተቀባይ አጡ ። ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ባወጀች ጊዜ ከእንግ
ሊዝ አገር ብቻ ሶስት ሺ ሰዎች ኢትዮጵያን ለመርዳት በወዶ ዘማችነት ተመዝግ
በው ነበር ። እ.ኤ.አ. ሴቴምበር 4 ቀን 1935 ዓም የወጣው ዴይሊ ኤክስፕሬስ
ጋዜጣ “…ንጉሡ ይህን እርዳታ አልተቀበሉትም ። ያልተቀበሉበትም ዋናው ምክን
ያት ለእነዚህ ሰዎች የሚከፈል ነገር የለም ብለው ነው ። ከኢትዮጵያውያን ጐን
ተሰልፈን እንዋጋለን ያሉት እንግሊዞች ብቻ ሳይሆኑ በራንግል አርሚ ውስጥ የነበ
ሩና ካገራቸው የከዱ ሩሲያውያን ፤ ቱርኮች ፤ ሁንጋሪያውያኖችና ቼኮዝሎቫኪያን

ሁሉ ናቸው ።...” ብሏል ። ይህ ብቻ ሳይሆን በኒውዮርክ ከተማ ያሉ አሜሪካውያን በሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት የኢጣሊያን እድራጎት ተቃወሙ ። በማዲሰን አደባባይ የተሰበሰቡ ዘጠኝ ሺ አሜሪካውያን የሙሶሊኒን ፎቶግራፍ በማቃጠል ተቃውሞአቸውን ገለጡ ። በኢጣሊያ ውስጥም ቢሆን ሳይፈሩ እድራጎቱን የተቃወሙ ሰዎች ነበሩ ። በጀርመን ሲኒማ ቤቶችም የሙሶሊኒን ጦር ማጋዝና ማከማቸት የሚያሳየው “ኢትዮፒያ 1935” የተባለው ፊልም ለሕዝብ እየታየ ሕዝቡ ተቃውሞውን ይገልጽ ነበር ። በካይሮም የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች በየመስጊዱ ሕዝቡን እየሰበሰቡ ኢትዮጵያን በግፍ ከመጣባት መከራ እንዲያድናት እንዲፀልይ አዘዙ ።

ይህ ሁሉ ቢሆንም ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሪዎች ስህተትና በመሣሪያ እጥረት ድል እየሆነ ይሄድ ጀመር ። ባዶሊዮ ራሱ ሲመሰክር “... የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ዘመናዊና ባለሙሉ ትጥቅ ባይሆኑ ኖሮ ኢትዮጵያውያን የአድዋውን ድል እንደገና ይደግሙ ነበር ። በፓይለቶቻችን ታላቅ ተግባር ኢጣሊያኖች ድል ለማድረግ በቃን ።....” ብሏል ። ይህንንም ወደፊት በየጦሩ ግንባር እናገኘዋለን ።


———O———



የክብር ዘበኛ ጦር



ላገሩ ክብር የተነሳው ዘማች ።



ከዘመተው ሥልጡን ሠራዊት ጥቂቱ (አድዋ ላይ የተነሳ) ።



ከአይሮፕላኖቻችን አንዲቱ ፖቴዝ የምትባለዋ አይሮፕላን (መቀሌ የተነሣ) ።



ያን ዘመናዊ ጦር ለመመለስ መረብ ላይ የመሸገው ወታደር ።



በሰናኔና በለበን የዘመተው ሠራዊት በሰልፍ ሆኖ ።



አዲስ አበባ ውስጥ ዘማቹ በሰልፍ ሲያልፍ



አዲስ አበባ ውስጥ ዘማቹ ሠራዊት ሲጓዝ




የክብር ዘበኞችና የሆለታ ተማሪዎች የዘመቻ ጉዞ ተራቸውን ሲጠብቁ ።




በጋሪ ላይ ተጭኖ በአዲስ አበባ ከተማ ይዞር የነበረው የሴቶች መፈክር (ማንቃቂያ)

ወንዶች ንቁ ። እንኳንስ ወንዶቹ


አገራችንን ጠብቁ ። እንዋጋለን ሴቶቹ ።




የምሥራቁ ዘማች ወደ ሐረርጌ ለመጓዝ ባቡር ላይ ተሳፈረ።




የሆለታ ልጆችና የክብር ዘበኞች የመጨረሻ ሰልፋቸውን አዲስ አበባ ውስጥ አሳዩ።



የክተት አዋጅ ነጋሪት ተመታ ።



ያለው ታንኳ የሌለው ቅሉን ይዞ ዘመተ




ዘማቹ አዲስ አበባ ከተማን ለቀቀ ።



ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ ።



ልዑል ራስ ካሣ



ልዑል ራስ እምሩ